# የመጤነት መሰረት ላላቸው ሰዎች
# ስለ ኮሮና አዲስ የቴሌፎን መስመር

የኮሮና ቫይረስን በተመለከተ ለሚኖርዎት አጠቃላይ ጥያቄዎች በራስዎ ቋንቋ መልስ ለማግኘት እዚህ መደወል ይችላሉ። መስመሩ ዘወትር በሥራ ቀናት ከ 09.00 - 12.00 ሰዓት እና ከ 13.00 - 15.00 ሰዓት ክፍት ነው።

የቴሌፎን መስመሩ ላይ የባህል- ሰገር ማዕከሉ (Transkulturellt Centrums) የጤና ጉዳይ አማካሪዎች ተመድበው የኮሮና ቫይረስን አስመልክቶ ለሚቀርቡላቸው አጠቃላይ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ። አማካሪዎቹ አረብኛ፥ ሶማሊኛ፥ ፔርሺያን/ ዳህሪ /ትግርኛ/ አማርኛ እና ሩሲያኛ የሚናገሩ ናቸው።

መስመሩ በዚህ ቁጥር 08-123 680 00 ይደረስበታል፥ እና ደዋዩ መጀመሪያ አንድ ማብራሪያ በኢንግሊዝኛ ይሰማል፥ ትንሽ ቆይቶ እንዱሁ በአረብኛ ማብራሪያ ይከተላል። ከዚያ በኋላ ደዋዩ በሚሻውን ቋንቋ የተመደበውን ቁልፍ ቁጥር በመምረጥ ይጫናል።

መስመሩ በሚዘጋበት ግዜ፥ መልሶ የሚከፈትበትን ሰዓት በእንግዚዝኛና በአረብኛ ይግልጽና ጥሪውን ወደ 1177 እና 112 ሊያደርጉ እንደሚችሉ በማሳሰብ ይጨርሳል።

---

## አጠቃላይ ጥያቄዎች –
## የጤና ጥበቃ ማብራሪያዎች አይደሉም

የቴሌፎን መስመሩ የጤና ጥበቃ ጉዳይ ማብራሪያ የሚጠየቅበት ስላልሆነ አንድ ታማሚ በዚህ መስመር ደውሎ እርዳታ ሊያገኝ አይችልም። አንድ ግለሰብ እንዲያ ዓይነት ጥያቄ ካለው መደወል ያለበት 1177 ነው። ይህ መስመር አገልግሎት የሚሰጠው ጠቅለል ያለ ባህሪ ላላቸው ጥያቄዎች ሲሆን፥ የወረርሽኑን መዛመት ለመቀነስ ወሳኝ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡-

- ኮሮና ምንድን ነው?
- እንዴትስ ነው የሚተላለፈው?
- ራስን መከላከል የሚቻለው እንዴት ነው?
- የሚቻል ከሆነ፣ ሥራን ቤት ውስጥ መስራት የሚመከረው በምን ምክንያት ነው?
- ወረርኙን እንዴት መግታት ይቻላል?
- ለምንድን ነው አያቴን መጠየቅ የሌለብኝ?
- ኮሮናን የሚያድን መድሃኒት አለ ወይ?
- በተለያዩ ቋንቋዎች የሚሰጡትን መረጃዎች የት ማግኘት ይቻላል?

---

## ስለ ጤና ጉዳይ አማካሪዮች

አማካሪዎቹ አዲስ መጤዎችን በጤና ጉዳይ በማማከር የአስር ዓመታት ልምድ ያካበቱ ሲሆኑ ስለ ጤና ሆነ ስለ አኗኗር መስተጋብር መረጃ የሚሰጡት በራሱ በባለ ጉዳይ ቋንቋ ወይም በቀላል ስዊድንኛ ነው። እነሱ ራሳቸው የመጤነት መሰረት የነበራቸው ሲሆኑ የጤና እና የህመተኛ እንክብካቤ ወይም የህብረተሰብ ጤና ሳይንስ ስልጠና የወሰዱ ናቸው።

የዚህ ቴሌፎን መስመር መከፈት ዋና ዓላማ፥ 1177 Vårdguiden የሚሰጠው አገልግሎት ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላትና ጫናውንም ለመቀነስ፥ እንዲሁም ኢላማችን የሆነውን የህብረተስብ ክፍል፥ ማለትም መጤውን ለመድረስ ነው። አገልግሎቱ ከስቶክሆልም አስተዳደር ህክምና ጉዳይ (SLSO) የቴaሌፎን ድጋፍ ሰጪ ክፍል እና የጤና – የህክምና ክፍል ኃላፊ ጋር በመተባበር የሚቀርብ ነው።